# በውጭው ዓለም ያሉት የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያናት በሰበካ ጉባዔ ወይስ በቦርድ ይተዳደሩ?

## መግቢያ

ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን እስራኤላዊያን እግዚአብሔር አምላክን ማምለክ ሲጀምሩ መሪያቸው የነበሩት ሙሴና ካህኑ አሮን ነበሩ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የቤተ መቅደሱም ሆነ ማንኛቸውም የአገልግሎትና አስተዳደር የሚመራው በካህናትና እንዲሁም በነቢያቱ ነበር። ከዚያም አልፎ ከግብጽ ባርነት የወጡት በዚሁ በነቢዩ ሙሴ መሪነት ነበር።

በሐዲስ ኪዳን ጌታችን መድኃኒታችን ወደዚህ ዓለም መጥቶ ቅዱሳን ሐዋርያቱን መርጦ ወንጌለ መንግሥትን ሲሰብክ ሳለ "አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እመሠርታለሁ" (ማቴ 16፥16-18) እንዲሁም "ሂዱና አሕዛብን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው" ባለው መሠረት (ማቴ 28፥19-20) ክርስቶስ በደሙ የመሠረታት ቤተ ክርስቲያን ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ከዘመን ወደ ዘመን እያደገች ፣ ተስፋፍታ እዚህ ደረጃ ደርሳለች። ሐዋርያቱም ሲጠባበቁ የነበረውን መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ በትምህርታቸው ብዙ ሰው እያመነ ወደ እነርሱ ይገባ ነበር። "ሕዝቡም ያላቸውንም ንብረት እየሸጡ በሐዋርያት እግር ሥር ያኖሩ ነበር ፤ እነርሱም ማናቸውም እንደሚፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉት ነበር"(ሐዋ 4 ፤35)። ሁሉም ሐዋርያት በየሀገረ ስብከታቸው አዲሲቱን ቤተ ክርስቲያን ይመሩ ነበር። ከሐዋርያቱ በኋላ በአንብሮተ ዕድ ተሹመው የተነሱት አባቶችም ለዘመናት ቤተ ክርስቲያን በመምራት የክርስትና እምነት አድጎ እዚህ እደረሰበት ደረጃ እንዲደርስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

## የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን

የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ጥንታውያን ከሚባሉት አንዷ ስትሆን ክርስትና የሀገራችን ዋና እምነት የሆነው ከአራተኛ ክ/ዘመን ጀምሮ ነው። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያናችን የራሷን ጳጳሳትና ፓትርያርክ መሾም የጀመረችው በዚህ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ነው። የመጀመሪያዎቹ አራት ጳጳሳት ግንቦት 25 ቀን 1920 በካይሮ ሲሾሙ የመጀመሪያው ፓትርያትክ ደግሞ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በ1951 ሢመተ ፕትርክናቸውን ካይሮ በሚገኘው የቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ፈጽመዋል። በግብጽ ስር በነበርን ጊዜ

አብያተ ክርስቲያናቱ ይመሩ የነበሩት እንደ አሁኑ በሰበካ ጉባዔ ወይም በቦርድ አልነበረም ነገር ግን በራሳቸው በካህናቱ ነበር። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያናችን ራሷን ከቻለች በኋላ እያደገች ስትሄድ ፤ አገልጋዮቿም እየበዙ በመሄዳቸው ከአገልግሎታቸው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አበል ለመክፈል ባለመቻሏ ምእመናኑም የበለጠ ተሳትፎ እንዲኖራቸው በማሰብ ግንቦት 1 ቀን 1963 ዓም የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ሁለተኛ ፓትርያርክ ሆነው የተሾሙት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤን መሥርተው በሀገራችን የሚገኙ ሁሉም ቤተ ክርስቲያኖች በቃለ ዐዋዲ እንዲመሩ አድርገዋል።

## <u>ሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ምንድን ነው?</u>

የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ በአጥቢያው ወይም ቤተ ክርስቲያኗ የአጠቃላይ መንፈሳዊ ጉባኤ (የካህናት ፣ ምዕመናንና የሰንበት ት/ቤት) አባላት የሚመሠረት የቤተ ክርስቲያኗ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ነው። ይህ አጠቃላይ ጉባዔ ከሰበካ አስተዳደር ጉባኤ በተጨማሪ ሌሎች በሥሩ የሚሠሩ ኮሚቴዎችንም ያቋቁማል። ቃለ አዋዲው ለረጅም ዓመታት ሲሠራበት የቆየ ሲሆን ተደጋግሞ ተሻሽሏል ነገር ግን ከዋናው መሠረታዊ ሐሳብ አልወጣም። የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አባላት ቁጥር እንደ አካባቢው ሊለያይ ቢችልም አመራረጡ ግማሹ ከካህናት ወገን ግማሾቹ ደግሞ ከምዕመናንና ከወጣቶች እንዲሆን ያዛል። የካህናቱና የምዕመናን ቁጥር እኩል የሚሆንበት ምክንያት በአንዳንድ ምሥጢራዊ ቤተ ክርስቲያን (ለምዕመናን የማይነገሩ) ጉዳዮች ላይ ካህናቱ ብቻቸውን ለመወሰን እንዲያስችላቸው በማሰብ ነው። ይኽ ቃለ ዐዋዲ ወጥቶ በሥራ ላይ ከዋለ ጀምሮ ምእመናን የበለጠ ኃላፊነት ተሰምቷቸው ፤ ቤተ ክርስቲያናቸውን የበለጠ እንዲያገለግሉ መንገድ ከፍቷል። እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን በሀብቷ እንድታድግ ፣ ስብከተ ወንጌል እና የበጎ አድራጎት እንቅስቃሴ የበለጠ እንዲስፋፋ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

በኢትዮጵያ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ቋሚ የሆነ የገንዘብ ያዥ ፣ የንብረት ኃላፊ ፣ የስብከተ ወንጌል ክፍል እንዲሁም ጸሐፊ ይኖረዋል። የሚመረጡትም የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አባላት ዋናው ኃላፊነታቸው አስተዳደራዊ ሥራ በትክክል መሠራቱን ፣ ገንዘቡ በሥርዓት ጠቀሜታ ላይ መዋሉን የመሳሰሉትን ነገሮች ይቆጣጠራሉ። አዳዲስ ዕቅዶችን ይነድፋሉ እንዲሁም እንዲፈፀም ያደርጋሉ። የቤተ ክርስቲያኗ ጸሐፊም በሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ስብሰባ እየተገኘ ቃለ ጉባኤ ይይዛል። የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳዳሪ በቀጥታ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ሊቀ መንበር ይሆናል። ይኽ ከላይ የተገለፀው አሠራር በኢትዮጵያ የተለመደ ሲሆን ነገር ግን ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚቋቋሙ አብያተ ክርስቲያናት ቤተ ክህነት በእንግሊዘኛ የተዘጋጀ መመሪያ አውጥቶ በመላክ የቃለ ዐዋዲውን መሠረታዊ ሐሳብ ሳይለቁ ከሚኖሩበት ሀገር ጋር እንዲሄድ አድርገው የራሳቸውን መመሪያ አዘጋጅተው እንዲጠቀሙበት አድርጓል። ።

## <u>ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያ ውጭ</u>

የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ከሀገራችን ውጭ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመችው በምድረ ቅድስት ኢየሩሳሌም በአራተኛው ክ/ዘመን ነው። ደጋጎቹ አባቶቻችን በዚያ ዘመን ሄደው ጌታችን ወደ ዓለም መጥቶ በተወለደበት በቤተልሔም ፣ በተጠመቀበት በዮርዳኖስ ፣ በተሰቀለበት ቀራንዮ እንዲሁም ልዩ ልዩ

ተአምራት በፈፀመባቸው ቦታዎች ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በማቆም ለእኛ እንዲቆይልን አድርገዋል። ከዚያም ከ1500 ዓመታት በኋላ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ሲነሳ ወገኖቻችን በተሰደዱ ጊዜ ፤ ቤተ ክርስቲያንም መንጋዎችዋን ተከትላ በሱዳን ፣ ኬንያ ፣ ጅቡቲ እና በእንግሊዝ ሀገር በባዝ ከተማ በጊዜያዊነት ተቋቁማ ነበር። ይሁን እንጂ ነፃነት ተመልሶ ሁሉም ወደ ሀገሩ ሲመለስ ቤተ ክርስቲያንም ተመልሳለች። ነገር ግን ኢትዮጵያን የሚወዱ የካረቢያን ተወላጆች የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን በሀገራቸው እንድትመሠረትላቸው በጠየቁት መሠረት በካረቢያንና በአሜሪካ በ1950ዎቹ ተመሠረተች። እንደዚሁም በእንግሊዝ ሀገር ከሚኖሩ የካረቢያን ተወላጆች ተመሳሳይ ጥያቄ ስለ ቀረበ እ.ኢ.አ በ1967 በአውሮጳ ቀደምትነት ያላት ቤተ ክርስቲያናችን ተመሠረተች። ቤተ ክርስቲያንም ሐዋርያዊ ተልዕኮዋን በመወጣት እነዚህን የካረቢያን ዜጎች በማስተማር ፣ በማጥመቅ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲጎለምሱ ከማድረጓ ባሻገር ከመሐከላቸው ለድቁና እና ቅስና ማዕረግ አብቅታ ቤተ ክርስቲያናቸውን እስከ አሁን እያገለገሉ ይገኛሉ።

አረመኔው ወታደራዊው ደርግ የዘውድ አገዛዝን ገልብጦ ወደ ሥልጣን ላይ በወጣና ኢሰብአዊ ድርጊት መፈጸም ሲጀምር ፤ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ለስደት ተዳረጉ። ከእነዚህም መካከል አንዳንዶቹ ዕድለኛ ሆነው ቤተ ክርስቲያን ተቋቁማ ባለችበት ሀገር ስለመጡ ፤ ወደ ቤተ ክርስቲያኗ በመምጣት ግልጋሎቱን በመጠቀምና በማገልገል መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ለማጠንከር ችለዋል። ሌሎች ደግሞ የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ባልተቋቋመችበት የመጡት ተሰባስበው ካህናት በማስመጣት ቤተ ክርስቲያን በማቋቋም የተለመደው አገልግሎት በውጭው ዓለም እንዲስፋፋ አድርገዋል።

## <u>የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን በአውሮጳ ፣ በአፍሪቃ ፣ በመካከለኛው ምስራቅና አውስትራሊያ</u>

ከላይ እንደጠቀስነው ቤተ ክርስቲያናችን በአውሮጳ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመችው እ.ኢ.አ በ1967 በአባ አረጋዊ ወ/ገብርኤል (በኋላ አቡነ ዮሐንስ) በእንግሊዝ ሀገር ነው። በመጀመሪያ የመጡት ለካረቢያኑ ቢሆንም የኢትዮጵያውያን ቁጥራቸው ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ ስለመጣ ምዕመናኑ አገልግሎቱ በገዛ ሀገራቸው ቋንቋ እንዲሆን ስለፈለጉ የራሳቸው የሆነ ቤተ ክርስቲያን እ.ኢ.አ በ1980 መጀመሪያ ላይ አቋቋሙ። ቁጥራቸው አንስተኛ ሆነው የተመሠረተች ይህች የለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ወቅት በሳምንት በአማካኝ ከ700 ያላነሰ ምእመናን በእሁድ አገልግሎት ላይ የሚሳተፉ ሲሆን ፤ የራሳቸው ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ገዝተው አገልግሎታቸውን በበለጠና በሰፋ ሁኔታ እያካሄዱ ነው። በተጨማሪም እ.ኢ.አ ከ1982 ጀምሮ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር (ሰንበት ት/ቤት) በማቋቋም ወጣቶች ስለ ቤተ ክርስቲያናችንና የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተደርጓል።

በመከተልም ቤተ ክርስቲያናችን በሌሎች የአውሮጳ ከተሞች በጀርመን ፣ በስዊድን ፣ ስዊትዘርላንድ እንዲሁም በሌላው ክፍለ ዓለም ተቋቋሙ። አንዳንዶቹ ከተሞች ላይ የተመሠረቱት ቤተ ክርስቲያናት ለትምህርት በሄዱ ካህናት ሲሆን ፤ በሌሎች ሀገሮች ደግሞ ምእመናኑ በመሰባሰብ ማኅበር መሥርተው ካህን በማስመጣት ቤተ ክርስቲያናችን በውጭው ዓለም እንድታድግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል። እነዚህ በካህንም ይሁን በምእመናን አስተባባሪነት የተመሠረቱ ቤተ ክርስቲያናት ለሥራቸው ሆነ ለአስተዳደር ዋና መመሪያ አድርገው የሚመሩበት በኢትዮጵያ አገልግሎት ላይ ያለውን ቃለ ዐዋዲ

በመሆኑ ፤ የቤተ ክርስቲያኒቷ አስተዳዳሪ ሆነ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ሊቀ መንበር ሁልጊዜ የሚሆነው ከአገልጋይ ካህናት የተመረጠው ወይም ተሹሞ የመጣው ካህን ነው። በውጭው ዓለም ሆነ በሀገራችን ማንኛውም በሃይማኖት ሆነ በበጎ አድርጎት ስም የሚቋቋሙ ተቋማት እንደ እየሀገሩ ሕግ መመዝገብ ስላለባቸው ፤ በተጨማሪም በሀገር ቤት የምንጠቀምበት ቃለ ዐዋዲም ሆነ ቤተ ክህነቱ ከኢትዮጵያ ውጭ ላሉ ቤተ ክርስቲያኖች መመሪያ ብሎ ያዘጋጀው በቂ ስላልሆነ ፤ በየሀገሩ ያሉት ቤተ ክርስቲያናት ከቃለ ዐዋዲው ጋር የሚሄድ ወይም ደግሞ የሀገሩን ሕግ ከቃለ ዐዋዲው ጋር በማዋሐድ ተጨማሪ ሕግ በማዘጋጀት ቤተ ክርስቲያናቸውን ይመራሉ። ለዚህም ምሳሌ የምትሆነን የለንደን ደ/ጽ/ቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ናት። የቤተ ክርስቲያኒቷ ምእመናን (ጠቅላላ መንፈሳዊ ጉባኤ) የዚህን ሕግ አስፈላጊነት በማወቅ 12 አባላት ያሉት የሕግ አርቃቂ ኮሚቴ አቋቁሞ ሥራው እንዲሠራ ተደርጓል። ኮሚቴውም ከሁለት ዓመት በላይ ሲሠራ ቆይቶ ረቂቁን ለመረጠው ጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ፤ ማንኛውም ምእመናን ተገኝቶ በረቂቁ ላይ እንዲወያይ ዕድሉን ሰጥቶ ከዓመት በላይ ውይይት ተካሂዶበት በመጨረሻ በጠቅላላው ጉባኤ ፀድቆ ቤተ ክርስቲያኒቷ እየተመራችበት ይገኛል። ይህ ሕግ በሌሎች ሀገሮች ላሉ ቤተ ክርስቲያኖች አርአያ ሊሆን የሚችልና መንደርደሪያ ሐሳብ ይሰጣል ብለን እንገምታለን።
http://ethiopianorthodox.org/biography/constitution.pdf

## የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ

የኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን በአሜሪካ መቋቋም የጀመረችው ልክ አውሮጳ እንደተመሠረተችው ወታደራዊው ደርግ ሥልጣን ሲይዝ ኢትዮጵያውያን በተሰደዱ ጊዜ ነው። በመጀመሪያ የመጡት ለሀገሩ እንግዳ ቢሆኑም ቤተ ክርስቲያናቸውን ለመመሥረት ያላቸውን ገንዘብ በማፍሰስ ፣ ንብረታቸውን በማስያዝ ፤ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በመግዛት ፣ ካህናት በማስመጣት ቤተ ክርስቲያናችን በአሜሪካ እንድትመሠረትና እንድትስፋፋ ያደረጉ ወገኖች አሁንም ሳይሰለቹ በጉልበትና በገንዘብ ቤተ ክርስቲያናቸውን እያገለገሉ ይገኛሉ። በአሜሪካ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ቤተ ክርስቲያኖች የሚመሩት በሰበካ አስተዳደር ጉባኤ እና በቦርድ ሲሆን ፤ የቦርዱ አወቃቀር ግን በየግዛቱ ይለያያል። ለምሳሌ፦

1) በአንዳንዱ ግዛት ምንም ዓይነት ካህን በቦርድ ውስጥ አይገባም። ካህናቱን ቦርዱ ይቀጥራል ሲያስፈልግ ያባርራል። በሌላ አነጋገር ካህናቱ አስተዳደርን በተመለከተ ጣልቃ አይገቡም።

2) በሌሎች ቦታዎች ደግሞ የቤተ ክርስቲያኗ ዋና አገልጋይ ካህን ከቦርድ ጋር በቅርብ ይሠራል ፤ ማለትም አብሮ ይሰበሰባል ፣ ጉባኤውን በጸሎት ይከፍታል። ነገር ግን ቃለ ዓዋዲው እንደሚያዘው ተጨማሪ ካህናት አብረው ገብተው አይሠሩም።

3) በሌሎች ግዛቶች ለምሳሌ በዋሽንግተን ዲሲ እንደሚገኘው የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የመሳሰሉት ደግሞ በቃለ ዓዋዲው መሠረት በሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ይተዳደራሉ።

እንግዲህ በአሜሪካ እንዲህ ዓይነት የተለያየ የአሠራር ሂደት እንዳለ እንመለከታለን። ይህ ወጥ ያልሆነ አሠራር በአንፃሩ በብዙ ቦታዎች ላይ ለሚፈጠሩ ችግሮች አንዱ ዓይነተኛ መንሥኤ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። በተለይ አንዳንድ በቦርድ የሚመሩ ቦታዎች አሠራራቸው እንደ ካምፓኒ ያለ ስለሆነ በአስተዳደር ውስጥ ያሉት አባላት ጥልቅ የሆነ የሃይማኖት ዕውቀት ስለሌላቸው ፤ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ በሚፈጠሩ ችግሮች ላይ የሚወስዱት እርምጃ እንደ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ስላልሆነ ብዙዎችን ሊያስቀይም ይችላል። አልፎ ተርፎም ምዕመናን ከቤተ ክርስቲያናቸው እንዲኮበልሉ ያደርጋቸዋል።

## በቦርድ የሚተዳደሩ አብያተ ክርስቲያናት ለምንድን ነው ወደ ሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አሠራር የማይመለሱት ወይም ደግሞ ሌሎች ከሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አሠራር ወደ ቦርድ መሄድ የሚፈልጉት?

እንግዲህ ከላይ እንዳየነው የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ እና የቦርድ አስተዳደርን ታሪካዊ አመጣጥና እንዲሁም በቦርድ የሚተዳደሩ አብያተ ክርስቲያናት ራሱ የተለያየ አሠራር እንዳላቸው ተመልክተናል። በዚህ ርዕስ ሥር ልዘረዝር የፈለኩት ቤተ ክርስቲያን በቦርድ እንድትተዳር አንዳንድ ምዕመናን ለምን እንደሚፈልጉ ዋና ዋናዎቹን ምክንያት ለማየት እንሞክራለን።

1ኛ/ አንዳንዶቹ ከመጀመሪያው ጀምሮ ቤተ ክርስቲያኗ ስትመሠረት ብዙ አስተዋፅኦ ከማድረግ ባሻገር ንብረታቸውን በማስያዝ የሚገለገሉበትን ቤተ ክርስቲያን መግዣ እንዲውል በማድረጋቸው የበለጠ ኃላፊነት ስለሚሰማቸውና የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደርና የገንዘብ አያያዝ በትክክል መካሄዱን ለማረጋገጥ ከልብ የሚያገለግሉ።

2ኛ/ በቤተ ክርስቲያኗ በቂ ካህናት ስለሌሉ ፤ ምዕመናኑ ስለሚበዙና በአስተዳደርም ከካህናቱ የበለጠ ዕውቀት አለን ብለው ስለሚያስቡ።

3ኛ/ ካህናቱ ሥልጣን ካላቸው ምዕመናኑን በቀላሉ ሊከፋፍሉ ይችላሉ ፤ በዚህም የተነሣ እነዚህ ተመራጮች የሚያስቡትን ዕቅድ ከግቡ ለማድረስ ዕንቅፋት ይሆናሉ ብለው ስለሚፈሩ።

4ኛ/ አንዳንዶች ደግሞ ቀድሞ በኢትዮጵያ እያሉ አጋጣሚው ፈቅዶላቸው ወይም ደግሞ በሙያቸው በአስተዳደር ሥራ ላይ የነበሩ ፣ የተከበሩ ፣ ነገር ግን በስደት ሀገር ያ ከበሬታ ከሌላው ማኅበረሰብ ማግኘት ስለማይችሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመምጣት በዚህ አመራር ኮሚቴ በመግባት በሀገር ቤት ያሳለፉትን ሕይወት ለማስታወስና የሕሊና እርካታ ለማግኘት ስለሚፈልጉ።

5ኛ/ አንዳንዶቹ ያሉባት ቤተ ክርስቲያን ከማንኛውም ሲኖዶስ እንዳትሆን ስለሚፈልጉ።

6ኛ/ አንዳንዶች ምንም እንኳ ደሞዝ ባይከፍልበትም ፤ ምናልባት ጥቅም ሊገኝበት ይችላል ብለው ስለሚያስቡ።

7ኛ/ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደሞ በአውሮጳ ያሉ ብዙ ሥራ ፈት ቤተ ክርስቲያኗን ስትተዳደር የነበረችበትን አሠራር አስወግደው እንደ ካምፓኒ አቋቁመው ለራሳቸው ሥራ የፈጠሩ መስሎ እንዲሰማቸው ስለሚልፈልጉ ፤ ሰላማዊ የነበረውን አካባቢ የሚበጠብጡ ፤

8ኛ/ አንዳንዶች ደግሞ በፖለቲካው መድረክ ወይም በማኅበረሰቡ የከሰሩና ተቀባይነት ያጡ ፤ ሌላ ቦታ ላይ ኢትዮጵያውያንን ማግኘት ያልቻሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመምጣት የሚበጠብጡ ፤

9ኛ/ ሌሎች ደግሞ ቦታውን ተጠቅመው ለሚፈልጉት ፖለቲካ ፓርቲ ለመደገፍ እንዲችሉ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## ማጠቃለያ

እንግዲህ ከላይ እንዳየነው ቦርድ የሚለው አስተዳደር በሁኔታዎች አለመመቻቸት በአጋጣሚ የተፈጠረ እንጂ በቤተ ክርስቲያን የተለመደ አሠራር እንዳልሆነ ነው። ነገር ግን መጀመሪያ ላይ እንደተመለከትነው መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ከወረደ ጀምሮ ከትምህርታቸው ባሻገር ቤተ ክርስቲያንን በአስተዳደር እንደመሩ ፤ ከእነርሱም በኋላ የተነሡ አባቶች እንዲሁ የእነርሱን ፈለግ ተከትለው እዚህ

የደረስንበት ዘመን እንዴት እንዳደረሱ እናያለን። ስለዚህ የካህናት በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ መኖር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ማለት ነው። የሆኖ ሆኖ በአሁኑ ወቅት ቤተ ክርስቲያን በሀገር ቤትና ከሀገር ውጭ ባለ ሲኖዶስ መከፈል ምክንያት ወጥ የሆነ አሠራር ለመመሥረት አስቸጋሪ ሆኗል። ነገር ግን ወደፊት ይህ ሁሉ ክፍፍል ቀርቶ በዓለም ላይ ያለችው ቤተ ክርስቲያናችን በአንድ ሲኖዶስ ስትመራ ፤ የዚያን ጊዜ ይህ የቦርድ አስተዳደር ሥርዓት ቀርቶ አብያተ ክርስቲያናቱ ወጥ በሆነ የሰበካ አስተዳደር ጉባኤ ፤ ካህናቶች በመሪነት የሚሳተፉበት ጊዜ ሩቅ ላይሆን ይችላል። መቼም ፈርዶብን በእናት ጀርባ ላይ ከታዘለ ሕፃን ጀምሮ እስከ አረጋውያን መሰደድ ከጀመሩ ዓመታቶች ተቆጥረዋል። ይኽ ደግሞ ካህናትንም ይጨምራል። ታዲያ እነዚህ አንዳንድ ካህናት አማራጭ ስለሌላቸው በስደት እንደ ተቀጣሪ ሆነው በመጠጋት ነገረ ዓለሙን ለቦርድ ትተው ኑሮአቸውን ቀጥለዋል። አንድ መኪና የተፈለገውን አገልግሎት እንዲሰጥ ሞተር እንደሚያስፈልገው ሁሉ ፤ አንድ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ካህናት ያስፈልጓታል። ምንም እንኳ አንዳንድ ካህናት ሥነ ምግባር ቢጎድላቸውም ከአምላካችን በታዘዝነው መሠረት እግዚአብሔር አምላካችንን በፍጹም ልንወደውና አገልጋይ ካህናቶቹን ልናከብራቸው ይገባል (መጽሐፈ ሲራክ 7 ፥29-30) እንጂ ፤ እንደ ማንም አልባሌ ሰው ካህናቱን እያስፈራሩ መናገር የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መቃወም ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችን ክፉን በክፉ አትቃወሙ (ማቴ 5 ፥39)ብሎ ስለሚያስተምረን እንዲሁም ራሱ አምላካችን ክፉ ካህናተ አይሁድ ገና ከመጀመሪያው አንስቶ እስከ ዕለተ ዓርብ እስከሰቀሉት ድረስ እንዴት በትህትና በፍቅር እንደታገሣቸው እያሰብን ፤ እኛም ካህናቱን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ስህተት ቢሠሩ በፍቅር ማየትና ግሣጼም ከሆነ ትህትና በተሞላው ሊሆን ይገባል።

ስለዚህ ምዕመናን በተቻለ አቅም በክርስቲያናዊ መንፈስ በመወያየትና በመከባባር ቤተ ክርስቲያናቸውን ከአገልጋይ ካህናቶቻቸው ጋር በመሆን ሊመሩ ይገባል። አሁንም አምላካችን አስተዋይ ልብን እንዲሰጠንና የመመስገኛ ቤቱን በትክክለኛው መንገድ እንድናገለግል የእርሱ ቅዱስ ፈቃድ ይሁን። አሜን።

www.ethiopianorthodox.org team!!

የካቲት 2004